የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

**ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፯**
**አዲስ አበባ ጥር ፳፰ ቀን ፪ሺ፯**

**በአዲስ አበባ ከተማ**
**ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ**

**Seventh Year No.67**
**Addis Ababa 5th February, 2015**


**ማውጫ**


የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ደንብ…………………ገፅ ፰፻፶፱


**CONTENTS**


ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT MELES ZENAWI LEADERSHIP ACADEMY REGULATION………………Page 859


## ደንብ ቁጥር ፷፯/፪ሺ፯

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ በየደረጃዉ በተለያዩ የስራ መስኮች በአመራር ኃላፊነት ተሰማርተዉ የሚገኙ የስራ መሪዎችን እንዲሁም የመንግስትና የልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችን የአስተዳደርና የሥራ አመራር አካላትንና ፈፃሚዎችን በአመራር ዕዉቀት፣ ክህሎትና ስነ-ምግባር ችሎታቸዉን በማነፅ የከተማው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕቅድ በሚገባ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የጎላ ሚና የሚጫወት አመራር ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በየደረጃዉ የሚገኘዉን አመራርና የአስተዳደር አካላትን የሥራ አመራር ዘይቤ በማሻሻል በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ብቁ እንዲሆኑ በማድረግ የሃገራችንና የከተማችንን የህዳሴ ጉዞ ዕዉን ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፤

## REGULATION No. 67/2015

## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHEMENT OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT MELES ZENAWI LEADERSHIP ACADEMY

**WHEREAS,** it has become necessary to equip, leaders of the Addis Ababa City Government who work at various levels as well as public and other work sectors, with leadership knowledge, skill and ethics so as to enable them play a vital role in the execution of the social and economic plans of the City;

**WHEREAS,** it has become necessary to realize the renaissance of the Country and the City by improving the leadership culture of leaders and organs of the City Administration at various levels which enabled them to be capable and competitive at the national and international level;


**ያንዱ ዋጋ**
**Unit price**

**አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭**
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

በስራ አመራር ዕዉቀት፣ ክህሎትና ስነ-ምግባር የታነጹ ተተኪ አመራሮችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት የሚያስችል የአመራር ሥልጠና አካዳሚ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፷፯/፪ሺ፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቻርተር"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ነው፤

፬. **"ከንቲባ"** ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፪(፫) እንደተተረጎመው የከተማ አስተዳደሩን የሚመራ ዋና ስራ አስፈፃሚ ነው፤

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish a leadership training academy which brings into being successor leaders equipped with leadership knowledge, skill and ethics in sufficient number and quality;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No.361/2003 and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012 the City Cabinet has issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Meles Zenawi Leadership Academy Establishment Regulation No. 67/2015".

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Regulation:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Charter"** means the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003;
4. **"Mayor"** means the Chief Executive Officer of the City Government as stated under Article 2(3) of the Charter;

፭. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ ነዉ፤

፮. "**የአመራር አካዳሚ**" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት የተቋቋመ የከተማው የአመራር ማስልጠኛ ተቋም ነው፤

፯. "**ቦርድ**" ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመና የአመራር አካዳሚውን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤

፰."**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. የፆታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ አመራር አካዳሚው መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር እና አቋም

## ፬. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ (ከዚህ በኋላ "አካዳሚ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. የአካዳሚው ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡፡

## ፭. ዋና መስሪያ ቤት

የአካዳሚው ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፡፡

5. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012;
6. **"Leadership Academy"** means the city leadership institution established under Article 4 of this Regulation;
7. **"Board"** means the highest management organ of the leadership Academy established in accordance with this Regulation;
8. **"Person"** means natural or legal person.

## 3. Gender Reference

Unless otherwise expressed expressions in this Regulation stated in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## PART TWO
## ESTABLISHMENT, OBJECTIVE, POWER AND FUNCTIONS AND ORGANIZATION OF THE LEADERSHIP ACADEMY

## 4. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Meles Zenawi Leadership Academy (hereinafter referred to as "the Academy") is hereby established as an independent City Government body.
2. The Academy shall be accountable to the Mayor.

## 5. Head Office

The Academy shall have its head office in Addis Ababa.

**፮. የአካዳሚው ዓላማዎች**

አካዳሚው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. በከተማ ልማት አጀንዳዎች ማለትም በመሬት ልማት፣ በከተማ ፕላን፣ በከተማ መሠረተ ልማት፣ በከተማ ቤቶች ልማት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት፣ በከተማ ትራንስፖርት፣ በመልካም አስተዳደር አጀንዳና በሌሎችም ዕዉቀት፣ ክህሎትና ብቃት ያለዉን አመራር መፍጠር፤

፪. በአስተዳደሩ በየደረጃዉ በአመራር ኃላፊነት ተመድበው ለሚገኙ አመራሮች በአመራር ዕዉቀት፣ ክህሎትና ስነ-ምግባር የታነፁ ሆነዉ እንዲወጡ ደረጃዉን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና መስጠትና ተተኪ አመራሮችን በብዛት እና በጥራት ማፍራት፤

፫. በየደረጃዉ የሚገኘዉን የከተማ አመራር በአመራር ጥበብ በማነፅ፣ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ብቁ እንዲሆን በማድረግ የሃገራችንና የከተማችንን የህዳሴ ጉዞ ዕዉን ማድረግ፤

፬. በዘመናዊ የጥናት፣ የምርምር፣ የምልከታ፣ የትንተና እና የሥርፀት ሥራዎች የተደገፉ ትምህርትና ሥልጠናዎችን በአስተዳደሩ በየደረጃው ላሉ አመራሮች በመስጠት በአስተማማኝ ማስረጃዎች የተደገፉ የበቁና የነጠሩ ሳይንሳዊና ችግር ፈች ሃሳቦችን የሚያመነጩ፣ ለሕዝብ የላቀ ተጠቃሚነት እምነት ያላቸው የከተማ አመራሮችን በብዛት እና በጥራት ማፍራት፡፡

**፯. አርማ**

አካዳሚው አላማውን የሚገልጽ አርማ ይኖረዋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**6. Objectives of the Academy**

The Academy shall have the following objectives:

1. creating leader with knowledge, skill and competence in the areas of urban development agenda like land development, urban plan, urban infrastructure, urban housing development, micro and small scale enterprises development, urban transport, good governance agenda and the like;
2. by providing education and training to leaders who are assigned at various levels of the City Government to equip them with leadership knowledge, skill and ethics; and to realize qualified and numerous successor leaders;
3. to realize the renaissance journey of the Country and the City by shaping leaders who are assigned at various levels with leadership wisdom and enable them capable and competitive at national and international level;
4. by providing education and training based on research, study, reflection, analysis and inculcation to leaders who are assigned at various levels to produce leaders in sufficient number and quality having deep belief in the well being of the people and capable of generating matured, scientific and problem solving thoughts.

**7. Emblem**

The Academy shall have its own emblem which shall reflect its objective; detail shall be determined by directive.

## ፰. የአካዳሚው ሥልጣንና ተግባር

አካዳሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የአስተዳደሩ አመራርና ሌሎች ፈፃሚ አካላት እንዲሁም ኅብረተሰቡ የትምህርትና የስልጠና ፍላጎትን መሰረት በማድረግ በሀገራችን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ዙሪያ በብቃት የሰለጠነ የአመራር ኃይል በጥራት ማፍራት የሚያስችል የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

፪. የከተማው እና የሃገሪቱን የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና መርሀ-ግብር ይቀርፃል በቦርዱ ሲፀድቅም በስራ ላይ ያዉላል፤

፫. የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ ለማሻሻል እንዲሁም የአመራሩን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚረዱ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ይሰራል፤

፬. የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና ሞጁሎች ያዘጋጃል፣ ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎችን ያደራጃል፤

፭. የመንግስትንና ሌሎች ተቋማትን አፈፃፀም ለማሻሻል የሚረዱ የተቋም ልማት ስራዎችን ይሰራል፤

፮. ለስልጠናው አግባብነት ያላቸው የስልጠና አሰጣጥ፣ የምዘናና ግምገማ ሥርዓቶችን ይነድፋል፤

፯. ከመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ወይም ተቋማት ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት በአመራር አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና ሥነ-ምግባር በተመለከተ ብቃትና ጥራት ያለው የአመራር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

## 8. Powers and Duties of the Academy

The Academy shall have the following powers and duties to:

1. provide short, medium and long term trainings on the policies and strategies of the country so as to produce capable leadership based on education and training demands of the public, leadership and executive organ of the City;
2. develop education and training curriculum of the Academy based on the policies and strategies of the City and Country and implement same up on approval by the Board;
3. undertake research and study activities that help to improve the education and training delivery of the Academy and the execution capacity of the leaders ;
4. prepare education and training modules and organize other education materials of the Academy;
5. undertake institutional development activities that help to improve execution capacity of the government and other institutions;
6. prepare training methodologies, assessment and evaluation systems relevant to the training;
7. provide qualified leadership training and consultancy services with respect to leadership thought, philosophy and ethics on the request of government offices or institutions or private organizations;

፰. ከከተማው አስተዳደር ባለሙያዎች የሥራ አመራር ብቃታቸዉን ለማጎልበትና ለማሳደግ የሚረዱ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል፤ ለሚሰጠዉ ስልጠና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፱. የከተማዉን ህዝብና ተቋማትን ችግር የሚፈታ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በቦርዱ ሲፈቀድ ያሳትማል፣ ያሰራጫል በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፲. ቦርዱ በሚያወጣዉ የምልመላ መስፈርት መሰረት ሰልጣኞችን ይቀበላል የዕለት ተዕለት ግንባታቸውን በመመዝገብ ይከታተላል፤

፲፩. የትምህርትና ስልጠና፣ የጥናትና ምርምር ክፍሎችን ያቋቁማል፣ እንዲሁም የትምህርትና የስልጠና መርጃ መሳሪያዎችንና መፃህፍት በማሰባሰብ የቤተ ሙከራና ቤተ መፃህፍትን በማደራጀት የስልጠና ሂደቶችን ያመቻቻል፤

፲፪. ሰልጣኞች ትምህርቱን ጨርሰው በስራ ሲሰማሩ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ የስልጠና ዉጤታማነት ጥናት ያካሂዳል፣ ለሚመለከተዉ አካልም ሪፖርት ያቀርባል፣ ከጥናቱ በመነሳት የተሻሉ የአሰራር ስልቶችን ይቀይሳል፤

፲፫. የተለያዩ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን፣ ወርክ ሾፖችን፣ ኮንፈረንሶችንና አውደ ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል ጥሪ ሲደረግለትም ይካፈላል፤

፲፬. ከሌሎች አቻ ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸዉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፣ ተሞክሮ ይለዋወጣል፤ ከነዚህ አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ ደረጃዎች ወይም ፕሮግራሞች ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት የእዉቅና ሰርተፍኬት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

8. prepare and provide short and medium term trainings to professionals of the City Government that help to improve their leadership capacity, and issue certificate up on completion;

9. conduct study and research activities that resolve problems of the public as well as institutions of the City, publish, disseminate and implement the findings thereon up on approval by the Board;

10. enroll trainees based on the requirement set by the Board and follow up their regular capacity building;

11. establish education and training, study and research departments, as well as organize teaching and training aid materials, books, library, and facilitate trainings;

12. follow up performance of trainees after completion of trainings, undertake research on the effectiveness of the training, report same to the concerned body and implement improved methodologies based on the findings of the research;

13. undertake educational seminars, workshops, conference, and participate up on invitation;

14. establish relationship and exchange good practices with Federal and Regional counterparts; issue or cause the issue of certificate of acknowledgement upon offering education and training at different levels or programs in collaboration with such bodies;

፲፭.የሥራ አመራር ሥልጠና፣ የምክር አገልገሎትና የጥናት ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ገቢ የሚያገኝባቸዉን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ ለሚሰጠዉ ትምህርትና ስልጠና አገልግሎት እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ የአገልግሎት ክፍያም ቦርዱ በሚያፀድቀው መጠን መሰረት ይሆናል፤

፲፮.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፯.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## ፱. የአካዳሚው አቋም

አካዳሚዉ ፡-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪. በከንቲባው የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፤

፫. ምክትል ዳይሬክተሮች፤

፬. የካዳሚክ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ)፤ እና

፭. አስፈላጊ የሆኑ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች፣ ይኖሩታል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የአካዳሚዉ የስልጣን አካላት አወቃቀር እና ሥልጣንና ተግባር

## ፲. የቦርድ አባላት

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩.ከንቲባው ………………………….…. ሰብሳቢ

፪.የከንቲባው የህዝብ ግንኙነት አማካሪ…………….…………….ምክትል ሰብሳቢ

፫. የአካዳሚው ዳይክተር…………… አባልና ፀኃፊ

፬. የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ…..…………..... አባል

፭.የፋይናንስና ኢኮኖሚያዊ ልማት ቢሮ ኃላፊ…….................................................አባል

፮.አንድ የአካዳሚው ምክትል ዳይሬክተር…..አባል

15. facilitate training, consultancy and research projects on leadership by which it can generate income and as appropriate, collect education and training service fees based on the rate approved by the Board;

16. own property, enter into contract, sue and be sued in its own name; and

17. perform other related activities in order to achieve its objectives.

## 9. Organization of the Academy

The Academy shall have:

1. A Board of Management (hereinafter referred to as the "Board'');
2. A Director General to be appointed by the Mayor;
3. Deputy Directors;
4. Academic Council (hereinafter referred to as the "Council''); and
5. the necessary departments and staff.

# PART THREE

# ORGANIZATION POWERS AND DUTIES OF ORGANS OF THE ACADEMY

## 10. Members of the Board

The Board shall have the following members:

1. Mayor ……………..………………..…..Chairperson
2. Mayor's Public Relations Advisor ………………..……..… Deputy Chairperson
3. Director General of the Academy ………………...……….. Secretary and Member
4. Head of Capacity Building Bureau………Member
5. Head of Finance and Economic Development Bureau…………………...……………….Member
6. One Deputy Director of the Academy …………………………..…….……..… Member

፯. የከንቲባው የህዝብ አደረጃጀት አማካሪ …..አባል

፰. የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት…አባል

፱. የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ……………………አባል

## ፲፩. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. የአካዳሚዉን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ተግባርና ኃላፊነቱንም መወጣቱን ያረጋግጣል፤

፪. የአካዳሚውን ዕቅድ፣ አደረጃጀት፣ የአሰራር ሥርዓት፣ እና ከዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡ የውሳኔ ሀሳቦችን እና ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ ያፀድቃል፤

፫. የአካዳሚዉን ልዩ ልዩ የአሰራር ስርዓቶችንና መመሪያዎችን ያፀድቃል፣ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤

፬. የአካዳሚውን ምክትል ዳይሬክተሮች ሹመት እንዲፀድቅለት ለከተማዉ ከንቲባ ያቀርባል፤

፭. ለአካዳሚው መሻሻልና ዕድገት የሚጠቅሙ ሀሳቦችን ያቀርባል፣ ምክርም ይሰጣል፤

፮. በአካዳሚዉ የሚቀርቡትን የስልጠናና የአቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮችንና ጥናቶችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፤

፯. የአካዳሚዉ የአካዳሚክ ሰራተኞች የሚተዳደሩበትን አጠቃላይ መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

፰. የአካዳሚዉን አርማ ያፀድቃል፤

፱. የአካዳሚውን የአገልግሎት ክፍያና ሌሎች መመሪያዎችን መርምሮ ያፀድቃል፤

7. Mayor's Public Organization Advisor …...Member
8. President of the Civil Service University …..…………………………….... Member
9. Head of Education Bureau …….. …..Member

## 11. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1. follow up the overall performance of the Academy and ensure the proper fulfillment of the duties and responsibilities of the Academy;
2. evaluate and approve plan, organization, work procedure and proposals and reports presented to it by the Director General;
3. issue procedures and directives of the Academy and follow up the implementation of same;
4. recommend for the appointment of Deputy Directors to the Mayor;
5. propose matters which are necessary for the effectiveness and strength of the Academy, and give advise;
6. evaluate and approve training and capacity building programs and studies;
7. issue the general directive to administer the academic staffs, and follow up the implementation of same;
8. approve emblem of the Academy;
9. determine service charge and other payment rates for the various services of the Academy;

፲. የአካዳሚክ ሰራተኞችን የደመወዝ እርከንና ጥቅማጥቅም ያስጠናል፣ በሚመለከተው የከተማ አስተዳደሩ አካል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፲፩. አካዳሚያዊ ጉዳይን በሚመለከት በማንኛዉም የአካዳሚዉ አካል ወይም በአካዳሚዉ የበላይ አካል በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ አካል የሚያቀርበዉን አቤቱታ መርምሮ የመጨረሻ ዉሳኔ ይሰጣል፤

፲፪. የአካዳሚውን አላማ ለማሳካት በሚረዱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፣ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

**፲፪. <u>የቦርድ ስብሰባ</u>**

፩. ቦርድ በየሁለት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፤

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

፫. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. <u>የቦርድ አባላት ተጠያቂነትና አበል</u>**

፩. ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ ሕግን በሚጥስበት ጊዜ ለሚያስከትለው ኃላፊነት በውሳኔው የተሳተፈ እያንዳንዱ የቦርድ አባል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሆኖም በሀሳብ የተለየ የቦርድ አባል በኃላፊነት አይጠየቅም፤

10. cause the study of the salary scale and other benefit schemes of the Academic staffs , and implement same upon approval by the relevant organ of the City Government;
11. hear and give final decision on grievances related to academic matters submitted to it on decisions of organs of the Academy;
12. perform such other activities as are necessary for the attainment of the objectives of the Academy.

**12. <u>Meeting of the Board</u>**

1. The Board shall meet once in two months; however, it may at any time hold an extraordinary meeting, whenever found necessary;
2. The presence of more than half of the members of the Board shall constitute a quorum;
3. Decisions of the Board shall be passed by majority vote; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of tie;
4. Without prejudice to the provision of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure regarding meeting.

**13. <u>Accountability and Allowance of Board Members</u>**

1. When decision of the Board violates the law, each member who has voted for shall be liable for what such decision entalils. However, a member who has dissented from such decision shall not be liable;

፪. እያንዳንዱ የቦርድ አባል ከአካዳሚዉ አበል የሚከፈለዉ ሲሆን የአበሉ መጠን በከተማዉ አስተዳደር ካቢኔ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፲፬. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፤

፪. ዋና ዳይሬክተሩ የአካዳሚው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከንቲባው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ. በዚህ ደንብ አንቀጽ (፰) የተመለከቱትን የአካዳሚዉን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. የአካዳሚዉ ዓላማዎች፣ መሪ እሴቶችና ድንጋጌዎች መከበራቸዉን ያረጋግጣል፤

ሐ. አካዳሚዉ ከፌዴራል፣ ከክልል አካዳሚዎችና አግባብነት ካላቸዉ ሌሎች ተቋማት ጋር ግኑኝነት እንዲፈጥር ያደርጋል፤

መ. የአካዳሚዉን የትምህርት ክፍሎች የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓቶችን ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ በስራ ላይ ያዉላል፤

ሠ. በአካዳሚዉ የሚሰጡ የአመራር ስልጠናዎች በሀገሪቱና በከተማው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤

2. Each member of the Board shall receive allowance from the Academy; and the amount of such allowance shall be determined by the Cabinet of the City Governmnet.

## 14. Powers and Duties of the Director General

1. The Director General of the Academy shall be accountable to the Mayor;
2. The Director General shall be the Chief executive officer of the Academy and direct, administer and control the activities of the Academy based on the general direction of the Mayor;
3. Without prejudice to the generality stated in sub-article (2) of this Article, the Director General shall have powers and duties to:
   a. exercise the powers and duties of the Academy specified under Article (8) of this Regulation;
   b. ensure the observance of the objectives, basic principle and values of the Academy;
   c. cause the Academy to create relationship with Federal, Regional and other counterparts;
   d. submit to the Board the organization and work procedure of the Academy, and implement same upon approval;
   e. ensure that the leadership training of the Academy are focused on the policies and strategies of the Country and the City;

ረ. የአካዳሚዉን የአስተዳደር ሰራተኞች በአሰተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሰ. የአካዳሚዉን የረዥምና የአጭር ጊዜ የሥራ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ መርሐ-ግብርና በጀት ያዘጋጃል፣ ለቦርዱ አቅርቦ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሸ. አካዳሚዉ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ቀ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚዉን ይወክላል፤

በ. የአካዳሚዉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፬. ዋና ዳይሬክተሩ ለአካዳሚዉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአካዳሚዉ ሌሎች ሃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፭.የምክትል ዳይሬክተሮች ተጠሪነትና አሿሿም

፩. አካዳሚው ምክትል ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፤
፪. ምክትል ዳይሬክተሮቹ በቦርዱ አቅራቢነት በከንቲባው ይሾማሉ፤
፫. የምክትል ዳይሬክተሮች ተጠሪነት ለዋናው ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

## ፲፮. የምክትል ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር

የአካዳሚዉ ምክትል ዳይሬክተሮች፡-

፩. የአካዳሚውን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳሉ፤

f. employ, administer and dismiss administrative staffs of the Academy in accordance with the civil service laws of the City Government;

g. prepare and submit to the Board long and short term plan, annual program and budget of the Academy, and implement same upon approval;

h. effect expenditure and open account in accordance with the approved budget and work program of the Academy;

i. represent the Academy in its dealings with third parties;

j. prepare and submit to the Board performance and financial reports of the Academy.

4. The Director General may delegate part of his power and functions to other officials and employees of the Academy to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Academy.

## 15. Accountability and Assignment of Deputy Directors

1. The Academy shall have Deputy Directors;
2. The Deputy Directors shall be appointed by the Mayor upon recommendation of the Board;
3. The Deputy Directors are accountable to the General Director.

## 16. Powers and Duties of the Deputy Directors

Deputy Directors of the Academy shall:

1. assist the General Director in planning, organizing, directing and coordinating the functions of the Academy;

፪. በአካዳሚው መዋቅራዊ አደረጃጀት ጥናት መሰረት ተለይተው የሚሰጣቸውን የስራ ክፍሎች ይመራሉ፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዳይሬክተሩ ወይም በከንቲባው ተለይቶ ሲወከል የተወከለዉ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

፬. በዋና ዳይሬክተሩ ወይም በቦርዱ ተለይተው የሚሰጡዋቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ፡፡

## ፲፯. <u>አካዳሚክ ጉባኤ</u>

፩. የጉባኤው ተጠሪነት ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፤

፪. የጉባኤው አባላት ቁጥርና ስብጥር በቦርዱ ይወሰናል፡፡

## ፲፰. <u>የጉባኤው ስልጣንና ተግባር</u>

ጉባኤው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. በቦርዱ የሚወጡትን መመሪያዎችና አቅጣጫዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. የሰልጣኞችን አቀባበል፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰንና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን የሚመለከቱ፡ መመዘኛዎችን ያወጣል፣ በነዚሁ አፈፃፀም ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

፫. የሰልጣኙን አጠቃላይ የመግቢያና የመውጫ ፈተና አሰጣጥ ደረጃዎች ይወስናል፤

፬. በቦርዱ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ የሰልጣኙን አስተዳደር፣ ትምህርት ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎች የምርጫ ሥነ-ስርአት፣ የመምህራን ቅጥር፣ እድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፕሊንና ደሞዝን በተመለከተ ይከታተላል፤

2. lead departments specifically entrusted to them in accordance with the organizational structure of the Academy;
3. act on behalf of the General Director in his absence when specifically designated by the General Director or the Mayor;
4. discharge such other duties which may be specifically entrusted to him by the General Director or the Board.

## 17. <u>Academic Council</u>

1. The Council shall be accountable to the Director General;
2. The Board shall fix the number and composition of members of the Cuncil.

## 18. <u>Powers and Duties of the Academic Council</u>

The Council shall have the following powers and duties:

1. Implement the directive and directions issued by the Board;
2. Issue the criterion for the admission of trainee, the educational level and descipline cases and investigate and determine complaints raised on same;
3. Determine the levels of administering enterance and exit exams of the trainee;
4. Follow up the administration of the trainees, academic matters, the election of academic heads, the employment, promotion, benefits, discipline and salary of the academic staffs in accordance with the direction of the Board;

፭. የአካዳሚውን ልዩ ልዩ የትምህርትና ስልጠና መርሀ-ግብሮች መርምሮ ያፀድቃል፡፡

**፲፱. <u>የጉባኤው አሰራር</u>**

የጉባኤው የአሰራር ሥርዓት ጉባኤው በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳. <u>በጀት</u>**

የአካዳሚው በጀት በከተማው አስተዳደር የሚመደብ፣ ከውስጥ ገቢ፣ እና ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡፡

**፳፩. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩. አካዳሚው የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. አካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፤

፫. የአካዳሚው የሂሳብ መዝገብ፣ ገንዘብ እና ንብረት ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ የከተማው አስተዳደርን ሕጎች የተከለከለ ይሆናል፡፡

**፳፪. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ መከበር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

5. Examine and approve the various education and training schedule of Academy.

**19. <u>Procedure of the Council</u>**

Rule of procedure of the Council shall be determined by the directive issued by the Council.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**20. <u>Budget</u>**

Budget of the Academy shall be from one allocated by the City Government, from internal income, and other legal sources.

**21. <u>Books of Accounts</u>**

1. The Academy shall keep complete and accurate books of accounts;
2. The books of accounts and financial documents of the Academy shall be audited annually by the Auditor General of the City;
3. The keeping and maintenance of the books of account, financial and property documents of the Academy shall comply with the laws of the City Government.

**22. <u>Duty to Cooperate</u>**

Any person shall be duty bound to cooperate for the implementation of this Regulation.

## ፳፫. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩. ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቦርዱ ሊያወጣ ይችላል፤

፪. አካዳሚው ይህን ደንብ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወጣውን መመሪያ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚረዳውን ዝርዝር የአሰራር ማኑዋል ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፳፬. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፱ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፳፭. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የአዲስ አበባ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለተቋቋመዉ አካዳሚ ተላልፈዋል፡፡

## ፳፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፯ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥር ፳፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**



## 23. <u>Powers to Issue Directive</u>

1. The Board may issue directives for the implementation of this Regulation;

2. The Academy may issue detailed guideline for the implementation of this Regulation and the directives issued under sub-article (1) of this Article.

## 24. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1. The Addis Ababa City government Management Institute establishment regulation No.13/1999 is hereby repealed;
2. Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistent with matters covered by this Regulation shall have no effect.

## 25. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

The rights and obligations of the Addis Ababa City Government Managaement Institute are hereby transferred to the Academy established by this Regulation.

## 26. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force as of 6th day of February, 2015.

**Done at Addis Ababa,**

**This 5th Day of February, 2015**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**